የካናዳን ቀን፡ በኢትዮጵያዊነት፡ ስሜት!



ሰኔ 27, 2015 ዓ ም፣ በቫንኮበር፡ የኢትዮጵያን ኮሚኒቲ ባዘጋጀው ‘እንደጋገፍ’ ፕሮግራም ላይ የኮሚኒቲው ሊቀመበር አቶ በረከት ከበደ የካናዳ 148 ዓመቷ ስለሚከበር ሐምሌ 1, 2015 ዓ ም፣ በዝግጅቱ ሥፍራ እንድንገኝ መልክት አስተላለፈ። በካናዳ ብዙ ዓመታት ብኖርም በኮሚኒቲም ስም ሆነ በግል ተገኝቼ አላውቅም፤ ምክንያቱን ውስጤ ቢያውቀውም አውጥቼ ብናገረው ትርጉም አይሰጥም። ማስታወቂያው ሲነገር ከሌሎች ተጋበዦች ጋር በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን ነበር። ሲራክ በደስታ ከመቀመጫው ተነስቶ ‘ሥፍራውን አውቀዋለሁ አብረን እንሄዳለን’ አለኝ፤ ሲራክ ሲጋብዘኝ እንቢ ማለት አልችልም፣ በቫንኮበር ለሕብረተሰባችን መሰባሰብ የሚጥሩ ብዙ እንዳሉ ባውቅም ሲራክ ሲያደርግ የማይታይ ግን ትልልቅ ነገሮችን የሚያደርግ ነው፤ ለምሳሌ በአካባቢያችን የመጀመሪያው የአማርኛ ቋንቋ አገልግሎት ለሚሰጠው ሬዲዮ ጣቢያ $500.00 ዶለር አሰተዋጾ በማድረግ የዕድሜ ለክ አባል ነው፤ በቫንኮበር የመጀመሪያውን የሃይማኖት አባት ያስመጣው እርሱ ነበር፤ ልጁ አማርኛ ትናገራለች እስክታውን ታስነካዋለች፤ የሀገሩን ባህልና ወግ የሚወድ የሌላውንም ይወዳል በማለት ሳላመነታ የካናዳን ቀን ለማክበር በደስታ ተቀበልኩት፤ እኔና ሲራክ አብረን ቡና እንኳን ጠጥተን አናውቅም፤ ለቁምነገር ሀገርን ለሚመለከት ጉዳይ ግን ሩጫዬ የምሄደው ከእርሱ ዘንድ ነው፤ የካናዳ ቀን ምሳሌ ይሁናችሁ፤ ወደ አከባበሩ ልመልሳችሁ፤



የዝግጅቱ ሥፍራ (Steveson & No 1, Richmond) ነበር፤ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ደረስን፣ መኪና ማቆሚያ ሥፍራ ችግር ነበር፤ በጋራ አነስ ያለች አውቶቢስ ብንከራይ ጥሩ ይሆናል የሚል ሐሳብ  አቀረበ፣ ይህ ሰው ለሚመጣው ዓመት ከአሁኑ ማሰብ ጀመር በማለት ከራሴ ጋረ ተነጋገርኩ ። ከመከኒዋ ወረደን ስንጓዝ የማውቃት ልዩና ሌላ እህት ከበድ ያለ ዕቃ በወሳሳ ተሸክመው ይጓዛሉ፤ ሌላው ለሕብረተሰቡ አስተዋጾ በማድረግ የሚታወቀው ጌታቸውን ሰላምታ ተለዋውጠን እህቶቻችን የተሸከሙትን ተቀብለናቸው፤ ከሥፍራው ደረስን ፤ አንድ ወጣት ቆሟል፣ የእኛ ቁጥር 87ኛው ነው ብሎ ወደ ቁጥሩ አመለከተን፣ ከአንድ ሰዓት ጀምሮ ይጠብቀን እንደነበረ ነገረን፤የወጣቱ ጽናት  አደነኩ።

ግራ ተጋባሁ ወደ  ልዩ ጆሮ ጠጋ ብዬ  ‘ ከጸሐይ የምትጠለይበት ድንኳን የት አለ?’ በማለት ጠየኳት፤ ብዙም ዝርዝር ውስጥ አልገባችም፣ የሚሆነውን የማወቅ መስሏት ይሆን? ’በረከት ተሳቢውን ይዞ ይመጣል’ አለችኝ፤ በጭራሽ የሚሆነውን የማላውቅ መሆኔን ተቀብዬ ሁኔታውን በአንክሮ መመልከቴን ቀጠልኩኝ፤



አሥር ሰዓት ሲሆን የኮሚኒታችን ሊቀመበር በረከት ከበደ ከነቤተሰቡ ተሳቢ ያላት መኪና እየነዳ ከሥፍራው ደረሰ፤ ልዩ ይዛ የመጣችው ዕቃ ተፈታ ፤ የቡና ጀበናው፣ ሲኒው ኮሮቦቱ፣ የቡና ቁርስ ማቅረቢያው ሞሶቡ፣ በተሳቢዋ ላይ ተደረደረ፤ የምተቀመጥበት ቡርኩባው ተደላደለ፤ የማየው ሁሉ ዕንቆቅልሽ ሆነብኝ፤

በረከት ሁለት ትልልቅ የኢትዮጵያን ሰንደቃ ዓላማ አረጓዴ ቢጫ ቀዩን አምጥቶ ነድቶ የመጣትን  መኪና መላውን እንድንሸፈነው አደረገ፤ አልፎ አልፎ የካናዳን ሰንደቃ ዓላማን  (Maple Leaf) የያዙም ነበሩ። የፕሮገራሙ አስተባባሪው አድማስ  የሀገራችንን አበባ አዴ አበባ የሚመስለውን (Extent Mom) የሚባለውን  አምጥቶ በዓሉን ለማክበር ከነቤተሰባቸው ለመጡት እህቶች አደላቸው፤ ለወንዶቹ ብዛት

ያላቸው በእጅ የሚያዙ ለታዳሚው የሚታደሉ የካናዳን ሰንደቃ ዓላማ አስያዘን፤ ሕጻናት የሚያድሉት ከረሚላና ብስኩት ተሰጥቷቸው በደስታ ሺቅብ ቁልቁል ሲሉ ይታያሉ፤ በሀገሬ ልጅ ሆኜ ጥምቀተ ባሕር ወርጄ የተጫወትኩትን ዘመን አሰታወሰኝ፤ ዘመኑን ብነግራችሁ ዕድሜህ ስንት ነው? ልትሉኝ ነው፣ ልለፈው፤

እውነት ለመናገር እስካሁን የሚሆነውን በእርግጠኝነት መናገር አልችልም፤ አንድ ነገር ለእኔ ግለጽ ነበር፤ ‘የካናዳን  ቀን’ የምናከብረው በኢትዮጵያውነት ስሜት መሆኑን ነው፤ አድማስ  ለተመልካቹ  እንዳድል የሰጠኝን  የካናዳን ሰንደቃ ዓላማ  ሰቀበለው ልቤን ባር ባር አለው፤ ምክንያቱን ወረድ በዩ እገልጻለሁ፤

ያም ሆነ ይህ ጎልቶ የሚታየው የካናዳ ሰንደቃ ዓላማ ሳየሆን የኢትዮጵያ ሰንደቃ ዓላማ አረንጓዴ ቢጫ ቀዩ መሆኑ ቢያስደስተኝም፣ አላፊ አግዳሚው በካናዳ ቀን አመካኝተው ‘የኢትዮጵያን ቀን ነው እንዴ የሚያከብሩት’  ይሉን ይሆን ብዬ ፤ ሰንደቃ ዓላማ የተሸፈነችውን መኪና ላይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ አድማስ አድል ብሎ የሰጠኝን የካናዳን ሰንደቃ ዓላማ  ከፍ አድርጌ አሣያቸዋለሁ፤  አስሙሣይ እንዳትሉኝ ገጠመኝን ላውጋችሁ፤



ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ቫንኮበር ከመምጣቴ በፊት በኦንታሪዮ፣ ከምኖርባት አንድ ትንሽ ከተማ፤ አንድ ወገን የሚኖርበትን ሁለት ክፍል ያለው አፓርታማ ለእኔ አሰተላለፎልኝ ወደ ሌላ ከተማ ይዛወራል፤ አንዱን ክፍል ትምህረት ቤት አብረን ለምንማር ተማሪ አከራየዋለሁ፤ የሀገሬ ልጅ አንደ ጥቁርና ነጭ የምታሳይ ትቪና የካናዳን ሰንደቃ ዓላማ በጥሩ ዘንግ ላይ የተሠቀለ በትቪው ላይ ትቶ ሄዷል፤ ከፍሉን የሚጋራኝ ካናዳዊ ነው ፤ ማታ ተቀምጠን አንዳንድ ዜናዎች በቲቪው እንከታተላለን፤ ሁልጊዜ ይህቺ ሰንደቃ ዓላማ ከትቪው ላይ ወድቃ አገኛታለሁ፤ መልሼ አስቀምጣታለሁ፤ ወድቃ አገኛታለሁ፤ አስቀምጣታለሁ፤ ትንሽ

ነገሩ ገብቶኛል፤ ሆኖም ሰንደቃ ዓላማውን እዚያ አገኘሁት እንጂ እውነት ለመናገር አምጥች ለማስቀመጥ ሰሜቱ የለኝም፤ 1990 ዓ ም በጋ ነበር ፣ ኦሎፒክ በስፔን ባርሶሎና ይካሄዳል፣ የየአገራት ተወዳዳሪዎች በሰለፍ ሲያልፉ እንመለከታለን፤ የኢትዮጵያውያን ከጁቢቲ ቀጥለው ኩስስ ብለው ሲያልፉ አየሁኝ፤ የአበበ በቂላ ሀገር ልጆች እንዲህ አመድ ነፍቶባቸው ሰመለከት፣ እንባ አነቀኝ፣ ራሴን መቆጣጠር አቃተኝ፣ እንባ አይደለም፣ ደም ከዐይኔ የሚወርድ መሰለኝ፣ ይህ ካናዳዊ ትኩር ብሎ ተመልከተኝ፤ ሰሜን ጠርቶ ( I think you love your country, yes,) እንደወትሮው ወድድሩን ስንመለከት 10ሺ ሩጫ የደራርቱ ሰም ተጠራ፤ ሰሟን ሰምቼው አላውቅም፤ በዚያን ወቅት ሀገሬ በመታ መንገድ ላይ ስለነበረች የእርሷ መሸነፍ ደግሞ ሌላ ሐዘን ይዞብኝ እንዳይመጣ ሰጋሁ፤ ከመቀመጫዩ ላይ ተነስቼ ተቁነጠነጥኩ፤ ካናዳዊው በመገረም ይመለከተኛል፣ የኦሎፒያው አሰተዋዋቂ (Tulu of Ethiopia)ቱሉ ኦፍ ኢትዮጵያ እያለ ሲያስተጋብ ነፍስ ወጪ ነፍስ ግቢ ሆነ ፣ ካናዳዊውም አጀበኝ፣ ደራርቱ በእውነቱ ራሷ ኢትዮጵያ ሆና ታየችኝ፤ በስቴዲዮ ያለው ሕዝብ ከመቀመጫው ተነሣላት፤ እርሷም ሰንደቃ ዓላማችንን አረጓዴ ቢጫ ቀዩን ለብሳ ተዋበችበት ተሸሞነመነችባት ከፍ ብላ እንድትውለበለብ አደረገች፤ እውነትም ኢትዮጵያ እጆቿን ወደዓምላኳ ትዘረጋለች፤ ይህን የተመለከትው ካናዳዊ በጣም ቆንጆ ሰንደቃ ዓላማ አላችሁ፤ ለምን አይኖርህም? ብሎ ጠየቀኝ፤ አየህ ይህ ቲቪ ላይ ያስቀመጥከው ሰንደቃ ዓላማ ያንት አይደለም፤ የካናዳዊያን ነው፣ሌሎች መሰዕዋትነት የከፈሉበት ነው አለኝ፤ እውነቱን ነበር አባቴ ቅደመአያቴ ደማቸው አፈሰው በቀኝ ገዥዎች እንዳትያዝ ሲፋለሙ የነበሩት ይህችን አረንጓዴ ቢጫ ቀዩን አረማችው እንደሆነች ነገርኩት፣ ለአስተያየቱም አመሰገንኩት፤ ከቤተሰቡም አሰተዋወቀኝ ፤ እሰከ ዛሬ እንጠያየቃለን።



በዚህ በምኖርበት ቫንኮበር ከተማ በ የካቲት 2008 ዓ ም፤ የክረምት ኦሎፒክ ሲካሄድ የቀድሞው የኮሚኒታችን ሊቀመበር አቶ ከበደ ሃይለማሪያም አረጓዴ ቢጫ ቀዩን ሰንደቃ ዓላማችን በኦሎፒያ መንደር እንዲውለበለብ በማድረጉ ይታወሳል፣ ይመሰገናል። አድማሰ የካናዳን ስንደቃ ዓላማ ሲሰጥኝ ቀር ያለኝ ለዚያ ነበር። ያም ሆነ ይህ የተፈጠሩባትን ሀገር ሣይረሱ የቤተሰብን መሠረት ሣይዘነጉ ወይም ሳይክዱ ያሉበትን ማድነቁ፣ መቀበሉ፣ መሳተፉ ሰንደቃ ዓላማውንም ማውለብለቡ ጤነኛ ነው እላለሁ፤

ወደ ዝግጅቱ ልመልሳችሁ፣ 86ኛው ቁጥር የያዙት ሁለት የካዴት መኪናዎች ሲቀሳቀሱ፣ ቀጣዩ 87ኛው የእኛ ስለነበር አድማሰ መመሪያ ሰጠን፤ ልዩ አረንጓዴ ፡ቢጫ፡ ቀይ ከሐር ከተሠራ ዲሪያዋን ተጎናጽፋ፣ በብርኩባው ላይ ተቀመጠች፣ ጀበናው በማቶቱ ላይ በስተቀኟ አኑረዋለች፣ ሲኒዎቹ በረኮቦቱ ላይ




ተደርድዋል፣ የቡና ቁርስ ያለበት መሶብ ከጎኗ ጉብ ብሏል፣ ባለችበት ተሳቢ ላይ ሊቀመበራችንና ቤተሰቡ የሚጠጣ ውሃ የሚበሉ ኩኪዎች, የሚታደል ከረሜላ አምጥተው ደርድረዋል፤ የተሣቢው ግራና ቀኝ በኢትዮጵያና በካናዳ ሰንደቃ ዓላማ አሸብርቋል፣ ለጉዞው ዝግጅት ሆነ፣ ሊቀመበራችን በረከት ከበደ ወደመኪናዋ ገባ፤ አድማስ ጮክ ብሎ 'የኢትዮጵያን የቡና አፈላልን ባህል ለማስተዋወቅ ስለሆነ ከተሣቢዋ ራቅ ብላችሁ ተጓዙ' የሚል መመሪያ አስተላለፈ፤ ሴት እህቶቻችን በዚህ አገር አጠራር (Extent Mom) የሚባለውን አበባ እንደሀገራችን አዴ አበባ ቢጫነት ያለውን ዕቅፍ አበባ ይዘው ጎን ለጎን ልዩን አጅበዋት ጉዞ ሆነ፤ ሙዚቃው ተለቀቀ፣ ጭፈራው ቀለጠ፣ ከተጓዦቹ አንዱ የኢትዮጵያ ሰንደቃ ዓላማ የተጎናጸፈውን 'ቀነኒሳ በቀለ' በማለት ቀለደ፤ ሌላው ደግሞ አበባ የታቀፉትን እህቶች 'እቴ አበባ በሉ' የሀገሩን ትዝታ ተወጣ፤ ጉዞው ቀጠለ፤ በእውነቱ ያከበርነው የኢትዮጵያን ቤተሰብ ቀን ቢባል ስህተት አይሆንም፤ የሊቀመበራችን ቤተሰብ በፎቱ ማንሳቱ ሲሳተፉ ለባዓሉ የመጡ ቤተሰቦች ለዝግጅቱ ድርሻ ነበራቸው፣ ሕፃናቱ በሰነደቃ ዓላማው ዕደላ፣ የከረሜላ ስጦታ፤ የአበባው አበርክቶት፣ የተመልካቹ ጭብጭባ፣ አብሮ እስከታ ለመምታት መቃጣቱ ደስ የሚያሰኙ ነበሩ፤ የሀገራችንን የቡና አፈላል ባህል ከማስተዋወቁ በላይ ልዩ የሴቶቻችንን ገጽባህሪ፣ ረጋ ማለታቸው የሚነገርላቸውን በተግባር በከፍተኛ ግርማና መጎስ የተቆላውን ቡና በሚተነው ማዕዛ ግራና ቀኝ የተቀመጠውን ታዳሚ እያወደችው ከሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት በላይ ልዩ ተጓዘች፤ ይህን ሳላደቅ ባልፍ ሒሊናዬን ይጎዳዋል፤ እኔ ብቻ አይደለሁም በሺ የሚቆጠሩ ካሜራዎች ሲያነጣጠሩባት ውለዋል፤ ከመጀመሪያው እስከ መጫረሻው ልጁ ረዳቷ ሆና አንዳንድ ሐሣቦችን ስትለግሣት ተመልክቻለሁ፤በውጭ ሀገር በሕብረተሰባችን ውስጥ በግልም ሆነ በጋራ በጥሩ ተጀምሩ በጥሩ የተከናወነ ዝግጅት ለማየት የመጀመሪዬ ሣይሆን ይቀራል?። |ይህ የወጣቱ ትውልድ እየበዛ መምጣት ምክንያቱ ይሆን? ወደ (New Paradigm) ወደ አዲስ ክስተት መሸጋገሪያችን

ይሆን? የአዳ ዲሞ ዘመን እየተሟጠጠ የመጣ ይመስላል፣ ይህ ትውልድ ከእኛ የሚፈልገውን ማወቅ ግድ የሚልበት ወቅትም ይመስላል። የማስተባበሩ ተግባር በአድማስ ላይ መጫኑ በሙዚቃው በኩል መዛባት ተፈጥሮአል፣ ሻወር ገብቶ ውሃ እንደተቈረጠበት እስከታ መችዎቻችና ተመልካቹ ጭምር በጉጉት ረገብ ያሉበት ወቅት ነበር፤ ከጉዞው ማብቂያ ላይ ዳቦው ተቆረሰ ቡናው ተጠጣ፤ የካናዳ ቀን በኢትዮጵያውነት ሰሜት አከበርነው፤ የዓመት ሰው ይበለን ብለን ተለያየን።

ቫንኮበር, ካናዳ
ታደለ መኩሪያ
tadele@shaw.ca